## ማን ነኝ?

ብርሃኑ አንተነህ እባላለሁ። በትምህርት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ (ኢኮኖሚስት) ነገር ግን በዓለም ዙሪያ በየዕለቱ የምታዘባቸው ለሰው ልጅ የአሁን እና የወደፊት የጋራ ዕጣ ፋንታ ጠንቅ የሆኑ ሁኔታወች እና ተጓዳኝ አድራጎቶች በእጂግ የሚያሳስቡኝ ተራ ግለሰብ ነኝ። ባጭሩ ዓለም ሠላም የሰፈነባት እና ሁሉም የዓለም ሕብረተሰብ አባል ካለሥጋት የደስታ ተቋዳሽ የሚሆንባት ፍትሀዊ እንድትሆን እመኛለሁ። የድሕረገጼ (fitihlehulum.com) እና የዩትዩብ የቴሌቪዥን መስኮቴ ስያሜ ከዚሁ ዕምነቴ የመነጨ ነው።

## ከልጅነት እስከ ዕድገት በሕብረት ዘመቻ

ማንኩሣ በምትባል ያኔ የገጠር ቀበሌ ተወለድኩ። ፍቅር እስከመቃብርን ያነበበ ሁሉ ከማንኩሣ ጋር ከአሁን ቀደም እንደተዋወቀ አምናለሁ። ማንኩሣ ተወልጀ ልደግ እንጂ ከበዛብህም ሆነ ከአዲስ ዓለማየሁ ጋር ዝምድና የለኝም። በማንኩሣ ለመጀመሪያ ጊዜ በዛፍ ሥር የዘመናዊ (አስኳላ) ትምህርታቸውን ከጀመሩ 13 ብላቴናወች አንዱ ነኝ።

የፍትህ ወሳኝነት ከውስጣዊ ስሜቴ ጋር የተቆራኘው ከልጅነቴ ነበር። ፍትህን ትርጉሙን ቀርቶ ቃሉንም አላውቀውም ያኔ። ነገር ግን በአካባቢየ በሰወች መካከል በማስተውላቸው ልዩነቶች ደስተኛ አልነበርኩም። ሁልጊዜ ለምን የሚል ጥያቄ አዕምሮየ ውስጥ ይፈጥሩብኛል። ለምሳሌ ወንዶች ሴቶችን ለምን የበታች አድርገው ያያሉ? በሙያወች መካከል ለምሳሌ ቄሶች እና ዳኞች ሲከበሩ ገበሬ ለምን ተመጣጣኝ ክብር አይሰጠውም? ሸማኔወች፤ ቆዳ ፋቂወች፤ ብረት ቀጥቃጮች፣ ሸክላ ሠሪወች ለምን ዝቅተኛ እርከን እንዲኖራቸው ተፈረጁ? በሌላ በኩል የሚያውቃቸውን እና የሚጠቅሙትን ባለሙያወች (artisans) የሚንቅ ገበሬ የማያውቀውን ንጉሥ ለምን ያወድሳል፤ ያደንቃል፤ ያከብራል፤ በንጉሡ ይምላል? ሥርዓቱ፤ ሕጉ፤ ወጉ ከስሜቴ ጋር አልተጣጣመም። በጊዜው ከእኔ ስሜት ጋር የተስማማው በዕድሜ ላይ ብቻ የተመሠረተ አክብሮት (ታናሽ ታላቁን ማከበር) እንጂ ሌሎች ልዩነቶች አልተዋጡልኝም። እነዚህ እንቆቅልሾች የማላውቀውን እንዳውቅ ጉጉት አሳደሩብኝ፤ በወቅቱ እንኳን ጥያቄወችን የሚመልስልኝ የሚሰማኝን የማጫውተው ጎልማሳ (adult) በአካባቢየ አልነበረም፤ አመለካከቴ ከሁሉም ያፈነገጠ በመሆኑ ከመናገር መቆጠብን እመርጥ ነበር።

በአካባቢየ የነበሩ ጎልማሶች ከሚያወሩት የምክትል፤ የወረዳ፤ እና የአውራጃ አስተዳዳሪወች በሕዝቡ ላይ የሆነ ተፅዕኖ እንዳላቸው ተረዳሁ። ተፅዕኖው ምን እንደሆነ እና እንዴትም እንደሚተገበር ፍንጭ አልነበረኝም። ከዚህ የተገነዘብሁት ነገር ቢኖር አስተዳደር በሕዝቡ መካከል እኩልነትን ለመፍጠር ሚና ሊኖረው እንደሚችል ብቻ ነው።

በሰወች መካከል እኩልነት የማምጣት ምኞቴን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተግባራዊ ጥረት ጋር ለማቀናጀት የሞከርኩት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪወች መንግሥት (student government) አመራር አባል ሆኜ በተመረጥኩበት ጊዜ ነበር። የሕዝብ ግንኙነት መኮንን (Public Relations Officer) ስለነበርኩ ሕዝቡ የተማሪወችን እንቅስቃሴ ከመቀበል አልፎ ኢጋር እንዲሆን ታላቅ ሚና እንደተጫወትኩ አምናለሁ። እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ትምህርት ቤቱን አዘግቶ የተማሪወች እንቅቃሴ አመራሮችን ወደ አዲስ አበባ እንዲኮበልሉ ሲያደርግ በዘዴ ሾልኬ ቀርቸ እንቅስቃሴውን ለብቻየ መርቻለሁ። ከፖለቲካ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ለመተዋወቅ የሞከርኩት በዚህ ጊዜ ነበር ማለት ነው።

የፖለቲካ ምኞቴን ከተግባር ጋር ለማቀናጀት በሞከርኩበት ወቅት የገጠመኝ የመጀመሪያው ችግር በአንድ ጉዳይ (issue) ላይ ሰወች ያላቸው አስተሳሰብ ምን ያህል የተለያየ ብቻ ሳይሆን የተበታተነ መሆኑ ነበር።

የተለያዩ ሃሳቦቻች እያንዳንዳቸው ከጉዳዩ ጋር የተሳሰሩ (systematic) በመሆናቸው ተወያይተን ወደ መግባባት በመምጣት የምናቃልላቸው ናቸው። የተበታተኑ ሃሳቦች ግን በጉዳዩ ሳይሆን በባለቤቱ መሠረታዊ ባልሆኑ ግላዊ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ለጉዳይ መዳበር ወይም ለችግሩ መፍትሔ የሚያደርጉት አስተዋፅዖ የላቸውም። በዚያን ጊዜ ሰወች ለምን እንደዚያ እንደሚያስቡ አይገባኝም ነበር። ዛሬ ግን ያን የመሰሉ አስተሳሰቦች ሁሉ ከግንዛቤ እጥረት (ignorance) ወይም በግላዊ ፍላጎት ላይ ብቻ ከማተኮር (greed) የሚመነጩ መሆናቸው ግልጽ ነው።  ዛሬ ስገነዘበው በምርምሩ ዓለም ጫጫታ (White noise or simply noise) የሚባሉ ከጉዳዩ ጋር ያልተዛመዱ ክስተቶች መሆናቸው ነው።

የሃሳብ መለያየት እና መበታተን ችግሮች በሁለት ደረጃ ነበር ያጋጠሙኝ። በመጀመሪያ ከእራሴ በስተቀር የቀሩት የተማሪወች እንቅስቃሴ አመራሮች ኢሕአፓ በመሆናቸው አስተሳሰባቸው በነጻነት ከእያንዳንዳቸው የመነጨ ሳይሆን እንደደመራ ችቦ ተጠፍንጎ የተሰጣቸው ወደኋላ ወይም ወደፊት ወደ ግራ ወይም ወደቀኝ የማያፈናፍን ድርቅ ያለ አቋም አንጸባረቀብኝ። በበኩሌ ከመልማዩ መምህሬ ጋር በነበረኝ ውይይት በሃሳብ ስለአልተግባባን ድህ ወላጆቸን ሳልጠር ባላመንኩበት ጉዳይ ሕይወቴን ላለመሰዋት የእራሴን መንገድ መርጨ ነፃነቴን አውጃለሁ። ኢሕአፓ የተማሪውን እንቅስቃሴ ከማበረታታት ይልቅ ትምህርት ቤቱ እንዲዘጋ ብቻ ሳይሆን አመራሮች ወደ አዲስ አበባ እንዲኮበልሉ ወሰነ፣ አባል ነን በሚሉ ብላቴናወች እንደተነገረኝ። ሌሎች የአመራር ባልደረቦቸ ጥሪውን ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሲኮበልሉ እኔ ትግሉን ከተማሪወች ጋር ቀጠልኩ። በተወሰነ ደረጃ የሃሳብ ነፃነት አገኘሁ፤ ተማሪወችም ተባበሩኝ። በተማሪወች እና በሕዝቡ መካከል በጣም የተናበበ የጥምረት አብዮታዊ ድምጽ አሰማን።

በሌላ በኩል የመወያየት ዕድል ከገጠመኝ አንዳንድ የሕብረተሰቡ አባሎች ጋር የነበረኝ የሃሳብ ልዩነት የጠበቅሁት አልነበረም። እንዲያውም ፈታኝ (challenging) ነበር። ይህን ገጠመኝ በወቅቱ የሕብረተሰቡ ድክመት አድርጌ በመውሰዴ ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነ ነበር የተገነዘብኩት። አሁን ሳሰላስለው ግን ከእራሴ ውስን የማሕበራዊ እንቅስቃሴ ንድፈ ሃሳብ (social movement theory) ዕውቀት የመነጨ ነበር። ባጭሩ ሕብረተሰቡ የተፈላጊውን ለውጥ ዓላማ እና ስልት ያውቃል ብየ መገመት አልነበረብኝም። በዚያን ጊዜ እራሴም ጠለቅ ያለ ግንዛቤ አልነበረኝም። የእኛ እንቅስቃሴ በብሔራዊ ደረጃ ይካሄድ የነበረው ነውጥ አካል በመሆኑ የወታደሩ ጁንታ የተከሰተውን የለውጥ አመራር ክፍተት ተጠቅሞ ሥልጣኑን በእጁ ካስገባ በኋላ ባደረገው የበላይነት ቁጥጥር አብሮ ተዳፈነ።

## የዕድገት በሕብረት ዘመቻ (1974 - 1976)

ሁለት ክፍለ ሀገሮች ዘምቻለሁ (ጎጃም እና ወሎ)። በመጀመሪያ ጎጃም ውስጥ ሉማሜ የምትባል ያኔ ትንሽ ከተማ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባልደረቦቸ ጋር ዘመትኩ። አዝማቾቻችንም የኛው አስተማሪወች ነበሩ። እንደዘመትን የሥራ ክፍፍል በሚደረግበት ወቅት ተማሪወች እና አስተማሪወች በመስማማት ትምህርት ቤት እያለሁ እሥራ በነበረበት ጋዜጠኝነት እንድቀጥል መደቡኝ። አዎ ያልተለመደ ቢሆንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋዜጠኛ ነበርኩ። በዚህም ምክንያት ሌሎች ወደ ንዑስ ጣቢያወች ሲበተኑ እኔ ዋና ጣቢያው መቆየት ነበረብኝ። አብዛኛወች ዘማቾች ከደብረ ማርቆስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጣን ስንሆን አሥር ወይም አስራ ሁለት የሚሆኑ ከአዲስ አበባ የመጡ ባልደረቦች ነበሩ።

የሥራ ድርሻዎቸ በሦስት ዘርፎች ይመደባሉ። በጋዜጥኝነቴ በየንዑስ ጣቢያወች እየተዘዋወርኩ ያን ያክል ጠለቅ ያለ ባይሆንም የአካባቢ መለያ የሆኑ ታሪካዊ እና መልክዓምድራዊ ዕውነታወችን፤ ዘማቾች ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ያላቸውን መግባባት እና የአሠራር (የማስተማር) ዘይቤ ታዝቤ ሙገሣ እና አሽሙር ወቀሳ ያካተተ ጽሑፍ እያዘጋጀሁ በየወሩ መጨረሻ ላይ በሚደረገው የዘማቾች ጠቅላላ ስብሰባ

ላይ ማንበብ ነበር። የዚሁ ጋዜጣ አካል የሆነ ሌሎች ዘማቾች ስሜታቸውን ያለገደብ የሚገልጹበት ተንፍስ የሚል አምድ ነበረኝ። በሁለተኛው ዘርፍ የዋና ዘመቻ ጣቢያው ሪፖርት ጸሃፊ ሆኜ በየወሩ መጨረሻ ላይ የወሩን ክንዋኔወች፤ የወደፊት ዕቅዶች እና ያጋጠሙ ተፈታታኝ ሁኔታወች አጠቃልየ ደብረማርቆስ ለሚገኘው ከፍተኛ የዘመቻ ጽሕፈት ቤት ማቅረብ ነበር። በመጨረሻም ከተማሪወች መንግሥት አመራር ልምዴ የመነጨ ይመስለኛል በገበያ እና በየትኛውም የሕዝብ ስብስብ ባለበት አጋጣሚ ሁሉ በማደርጋቸው ንግግሮች የዘመቻውን ዓላማ መግለጽ እና ሕዝቡ በዕድሉ እንዴት ሊጠቀም እንደሚችል ማስረዳት ሦስተኛው ተግባሬ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ስንሠራ ከቆየን በኋላ ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር ያለንን መግባባት ለማጠንከር በአካባቢው ተሰሚነት ያላቸውን የተወሰኑ ግለሰቦች ለእራት ጋበዝን። ለእራት ስንዘጋጅ አንድ በግ ለክርስቲያኖች በቄስ ሌላ በግ ለእስላሞች በሸክ አሳረድን። እራት ተበልቶ እንደተለመደው ግብዣችንን አክብረው ለመገኘታቸው የምሥጋና ንግግር አድርጌ እንግዶችም አመስግነው ስንጨርስ እንግዶች ወደ እየመጡበት በመመለስ ላይ እያሉ ከድንኳኑ ውጭ እረብሻ ተሰማ። ፖሊሶች በአካባቢው እንዳሉ አስተዋልኩ፤ ስለሁኔታው ግን የማውቀው ነገር አልነበረም። በኋላ ፖሊስ ከተደበቅሁበት የመኝታ አዳራሽ ገባ እና “እንዴ! ሌሎች እርስበርሳቸው ሲደባደቡ አንተ እንዴት እዚህ ቁጭ ብለህ ታያለህ?” ሲል ጠየቀኝ፤ በየአደባባዩ ንግግር ስለማደርግ ኃላፊ መስየው። እኔም ምንም የማውቀው እና ላደርግ የምችለው ነገር እንደሌለ ስነግረው ጥሎኝ ወጣ። ፖሊሶች ሁኔታውን በቁጥጥር ሥር አዋሉት። እኔም በማግሥቱ ከአዲስ አበባ በመጡ ጥቂት ዘማቾች እና በሌሎች መካከል ውጥረት እንደነበረ እና ሌሎች ከአዲስ አበባ የመጡትን ሊያጠቁ እንደሞከሩ ከምክትል አዝማቿያችን እና አስተማሪያችን ሰማሁ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ዋናው የዘመቻ ጣቢያ ኀላፊያችን እኔ የማላውቀው የዘማቾች ስብሰባ ጠራ። ከዚያ በፊት የሚደረጉ ስብሰባወች ሁሉ በእኔ አስተባባሪነት ነበር የሚጠሩት። ስብሰባው ላይ እኔም ተገኘሁ፤ ስብሰባው ከምንተኛበት አዳራሽ ውስጥ ስለነበር። የዘመቻ ጣቢያው ዋና ኃላፊ ስብሰባውን ከከፈተ በኋላ ከጥቂት ቀናት በፊት ከአዲስ አበባ በመጡ ጥቂት ዘማቾች ለደረሰው ወገናዊ ጥቃት እኔን ተጠያቂ አድርጎ ለ”ጥፋቴ” ምን ዓይነት ቅጣት ይገባዋል ብለው እንደሚያስቡ ዘማቾችን በመጠየቅ ንግግሩን ደመደመ። ስለክሱ የሰማሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም አልደነቀኝም። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ትምህርት ቤቱን አዘግቶ የተማሪ መንግሥት አመራሮችን ወደ አዲስ አበባ ሲያስኮበልል አብሬ ከመኮብለል ይልቅ ከተማሪወች ጋር ትግሉን በመቀጠሌ የኮበለሉ ጀሌወች ጥርስ እንደነከሱብኝ እና ከአዲስ አበባ በመጡ ጥቂት ዘማቾች ላይ ወገናዊ ጥቃት የማድረሱ ሴራ በእነሱ የተጠነሰሰ እና የተቀነባበረ እንደ ነበር አውቃለሁ። ከእነዚህ ጀሌወች ውስጥ አንዱ ገበያ ላይ በሕዝብ ፊት እንድሰቀል ሲጠቁም ሌሎች የተማሪወች መንግሥት ፕሬዚዳንት የነበረውን ግለሰብ ጨምሮ የዘመቻ ጣቢያው የእኔን አገልግሎት እንዳያጣ በማሰብ በመለስተኛ ቅጣት እንድታለፍ ሃሳብ አቀረቡ። ከእነዚህ ሃሳቦች አንዱ የተማሪወች መንግሥት ፕሬዚዳንት የነበረው ግለሰብ በስፋቱ እና በጥልቀቱ በቁመቴ ልክ ጉዳጓድ ቆፍሬ አፈሩን በመመለስ ጉድጓዱን እንድሞላ ሲል የጠቆመው ቅጣት ነበር። ጀሌወች የቅጣት አማራጭ ሀሳቦቻቸውን ሰንዘረው ካበቁ በኋላ አሳቤን ለመስጠት ፍላጎቴን ስገልጽ የጣቢያው ዋና ኃላፊ አትችልም ሲል አስደነቀኝ። ከቅምጤ በመነሳት መድረኩ ከዚህ ቀን በፊት የእኔ እንደነበር እና የእሱም ኃላፊነቱ የሁሉንም ዘማቾች ደህንነት መጠበቅ እንደሚጨምር ገለጽኩለት እና መድረኩ ላይ ወጣሁ፣ እሱም ከመድረኩ ወረደ። ከዚያም ለጀሌወች እንኳን ልትሰቅሉኝ ወይም ጉድጓድ ልታስቆፍሩኝ አፍንጫየ ላይ ዝምብ ብታዩ ካለእኔ ፈቃድ ልታባርሯት አትችሉም ብያቸው ልቀመጥ ስል አስቀድሞ የተዘጋጀ የፖሊስ ኃይል ኖሮ ገቡ እና ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ። አንድ ቀን ካደርኩ በኋላ የክፍለ ሀገሩ ዘመቻ ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ ወደ ደብረ ማርቆስ ወሰዶ ተለዋጭ ሥራ እስኪያገኝልኝ ድረስ ከቀን አበል ጋር እረፍት ሰጠኝ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ የዘመቻ ጽፈት ቤት ተላክሁ። በግምት ሁለት ወር ያክል ከቆየሁ በኋላ ወደ ገጠር እንድመደብ ጠይቄ ወደ ወልድያ ወሎ ተላክሁ። የወልድያው ኃላፊ መርሳ መደበኝ። የመርሳ ኃላፊወች በነበርኩበት ምን እሠራ እንደነበር ሲጠይቁኝ በጋዜጠኝነት የሠራሁባቸውን ዘርፎች ነገርኳቸው። በሃሳቡ ተደንቀው በጋዜጠኝነት እንድቀጥል መደቡኝ። እኔ ግን ዘማቾች አውቀው ካልፈቀዱልኝ በጋዜጠኝነት ልሠራ እንደማልፈልግ ነገርኳቸው። ከዚያም የዘማቾች አጠቃላይ ስብሰባ ተጠራ። በስብሰባው የጣቢያው ኃላፊ የስብሰባውን ዓላማ ከገለጸ በኋላ ጋዜጠኛ ብሆን ምን እንደምሠራ ተንትኘ አስረዳሁ። በርከት ያሉ ጥያቄወች እና መልሶች ነበሩ። ይህንን ተከትሎ ዘማቾች ባንድ ድምጽ በጋዜጠኝነት ሥራየ እንድቀጥል ፈቀዱልኝ። ያ ከሆነ በግምት ሦስት ወር በኋላ ዘመቻው በብሔራዊ ደረጃ ተዘጋ።

ለተወሰነ ጊዜ ቡና ቤት እየሠራሁ ወልድያ ቆየሁ። ከዚያም ትምህርት ቤት ሲከፈት ወደ ደብረ ማርቆስ ተመልሸ ከመስከረም እስከ ጥር ድረስ ትምህርቴን ከተከታተልኩ በኋላ ፈተና ልንወስድ ስንል እንደገና ኢሕአፓ ትምህርት ቤቱን አዘጋው። ከመዘጋቱ በፊትም ሆነ በኋላ ምንም እንቅስቃሴ አልነበረም። የትምህርት ቤት መዘጋት በወቅቱ ሁኔታወችን አመሰቃቀለብኝ። ይረዱኝ የነበሩ ፈረንሳዮች በለውጡ ምክንያት ጓዛቸውን ጠቅለው ሄደዋል። ወደ ገጠር እንዳልመለስ እርሻ ልጀምር ነው። እርሻ ከጀመርኩ ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ዕድሌ ይመነምናል። ከተማ አካባቢ ለመቆየት ወሰንኩ። ሌላ አማራጭ በማጣቴ ከዘመቻ በኋላ ወደሠራሁበት ቡና ቤት ወልድያ ተመለስኩ። የጠበቀኝ ሁኔታ ወልድያ ለመቆየት የሚያበረታታ አልነበረም። ለጊዜው የጥጥ ለቀማ ሥራ አለ ሲባል ስለሰማሁ ከወልድያ ወደ አሳይታ ጉዞየን ጀመርኩ።

እሥራት እና ስቃይ (ከጥር 1977 እስከ መስከረም 1978)

ፖለቲካ ውስጥ ባልሳተፍም የወታደራዊ ጁንታውን የእሥራት እና ሥቃይ ወጥመድ አላመለጥኩም። ከወልድያ ደሴ ደረስኩ። ወደ አሳይታ የሚወስደኝን የመጓጓዣ አማራጭ እየፈለግሁ ባለሁበት ወቅት ለተወሰኑ ደቂቃወች ለማረፍ ደሴ ማዕከል ላይ ካለው የስልክ ቤት ገብቸ እንደአጋጣሚ ከዚያ በፊት ያየኋት የስልክ ተራዋን የምትጠባበቅ ፋርማሲስት ስላገኘሁ ሰላም አልኳት እና ከጎኗ ተቀመጥኩ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ይቅርታ ጠይቃኝ ወጥታ ከአንድ ቆዳው ጠቆር ካለ ረጅም ሰው ጋር ስታወራ አየኋት። እነሱም አንዳንዴ ወደ ውስጥ ይመለከታሉ። ዓይቻዋቻቸው እኔ ላይ ማረፉቸውን ግን አልጠረጠርኩም። ለመጠርጠርም ምክንያት አልነበረኝም። ሴትዮዋ ተመልሳ ካጠገቤ ቁጭ ካለች የተወሰኑ ደቂቃወች በኋላ ያነጋገረችው ሰው መጣ እና እንደሚፈልገኝ ነገረኝ። ለምን ስለው ምክንያት አልሰጠኝም። ይልቁንም አጣድፎ ከሕንጻው ከአስወጣኝ በኋላ እጆቸን በካቴና አሥሮ ደሴ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ከተተኝ። ፖሊሶች በጥብቅ እንድጠበቅ ተነግሮናል በማለት አብዛኛውን ጊዜ የማሳልፈው እጆቸ ከእግሮቸ ጋር ተጣምረው በመታሠር ነበር። የጊዜውን በሽታ ከመጠርጠር በስተቀር ለምን እንደታሰርኩ አላወቅሁም። ጊዜው እየገፋ እና ከፖሊሶችም ጋር እየተላመድኩ ስሄድ እግሬን ብቻ ታሥሬ አንዳንዴም ከካቴና ነፃ ሆኘ የማሳልፋቸው ሰዓታት ነበሩ። ከአጋጣሚወች አንዱን በመጠቀም ለማምለጥ በሠፈሩ ያሉ የተወሰኑ የግል መኖሪያ ቤት አጥሮች ከዘለልኩ በኋላ ተይዠ ወደ ፖሊስ ጣቢያው ተመለስኩ። እጆቸ ከእግሮቸ ጋር እንደገና ተጣመሩ። በጥይት ሳልመታ ወደ ጣቢያው መመለሴን ስገነዘብ በመጠኑም ቢሆን መታሠሬን እንዳላማርር እረዳኝ።

ካለምርመራ ከወራት ቆይታ በኋላ ሰው ሊገድል ሲተኩስ ከተያዘ የኢህአፓ አባል እና እሱ ካሳሠረው ጓደኛው ጋር ወደ ኮምቦልቻ እሥር ቤት ተወሰድኩ። ኮምቦልቻ የተወሰኑ ወራት ካሳለፍኩ በኋላ ከፍተኛ

ተብለው የተፈረጁ ወንጀለኞችን የሚመረምር ሦስት አባሎች ያሉት ቡድን ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ መምጣቱን ተከትሎ ከኢህአፓ አባሎች ጋር ወደ ደሴ ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተዛወርኩ። በማግሥቱ ደሴ የአልጋ ወራሽ ቤተመንግሥት ብለው ወደሚጠሩት ግቢ ለምርመራ ተወሰድኩ። የኢህአፓ በልደረቦችም አብረውኝ ነበሩ። መርማሪ ቡድኑ መጀመሪያ ሰው ለመግደል ሲተኩስ እጅ ከፍንጅ የተያዘውን የኢህአፓ አባል ወደ ምርመራ ክፍል ወሰዱት። እኔ እና ሌላው የኢህአፓ አባል መቆያ ክፍል ውስጥ ሆነን ተራችንን እየጠበቅን ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የተመረመረው ግለሰብ ተዝናንቶ እየሳቀ ተመለሰ እና መቆያው ክፍል ውስጥ ተቀላቀለ። እኔ ወደ ምርመራ ክፍል ተጠራሁ። መርማሪወች (የሕብ ደህንነት ይሏቸዋል) ስለ እኔ ሁሉን ነገር እንደሚያውቁ እና ከእኔ የሚፈልጉት ዕውነቱን እንደሆነ በመግለጽ ታማኝ ከሆንኩ እንደምፈታ ያለያ ግን እሥራቱ እንደሚቀጥል ነገሩኝ። እኔም በማነኛውም ደረጃ እና ሁኔታ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፌ እንደ ማላውቅ ነገርኳቸው። ዕውንቱን እንድናገር ጠይቀውኝ ዕውነቱን ስነግራቸው አልተዋጠላቸውም። ከተወሰኑ ጥያቄ እና መልሶች በኋላ አመረሩ። ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ከእኔ በፊት የተመረመረው ኢህአፓ የደሴ እና አካባቢዋ የኢህአፓ ተወካይ እንደሆንኩ እና የእሱ የኢህአፓ ግንኙነት በእኔ በኩል እንደሆነ እንደነገራቸው፤ ያለኝ አማራጭ ይህንን ማመን እና ከእሥር ቤት መውጣት ወይም መካድ እና ባለሁበት መቀጠል መሆኑን ነገሩኝ። እኔም ከኢህአፓ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለኝ አና አባሎችን ከነበርኩበት ፖሊስ ጣቢያ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ከዚያ በፊት እንደማላውቃቸው ነግሬ ከዚያ በኋላ ለ18 ቀናት የቆየውን የስቃይ (torture) ምርመራ ጀመርኩ። ከሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ እያመላለሱ እራሴን ወደ ታች እግሮቸን ወደላይ አድርገው በመስቀል ለ18 ቀናት ደበደቡኝ። እግሮቸ ደም ለብሰው እያበጡ መቆም ስለተሳነኝ ከመኪና ወርጀ ወደ ክፍሌ የምገባው እንደልጅነቴ በአራት እግሮቸ እየዳሁ ነበር። ጫማየ ሥር እስከ ዛሬ የሚያቃጥል ዶክተሮቸ ክሊኒካል ማብራሪያ (explanation) ያላገኙነት ስሜት አለኝ። በ18ኛው ቀን ላይ ተሰቅየ እየተገርፍኩ እያለሁ መሬት ተንቀጠቀጠች። መርማሪወች ተደናገጡ። እኔንም ከተሰቀልኩበት አወረዱኝ። ከዚያም መሪው “ይሄ ሰውየ አስማታም ነው፤ ቃሉን ተቀበሉ እና ወደ ውህኒ ቤት ላኩት” በማለት መመሪያውን ሰጠ ወደ እኔ እየተመለከተ። የመሬት መንቀጥቀጡ ኣጋጣሚ እና የሰውየው ደንቆሮነት ስቃየን በ18 ቀናት ብቻ ወሰኑልኝ። ቃሌን ሰጥቸ ከኢህአፓ አባሎች ጋር ወደ ደሴ ወህኒ ቤት ገባሁ። ያኔ ሁለተኛው የኢህአፓ አባል መርማሪወች ስለእኔ እንደጠየቁት እና ዕውነቱን ማለት እኔን ጓደኛው እንዳለው ሳይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኝ ፖሊስ ጣቢያ መሆኑን እንደነገራቸው አጫወተኝ። የተገደለው ጓደኛው ያስገደለኝን ይሄኛው ዕውነቱን በመናገር ከሞት አተረፈኝ።

በደሴ ከርቸሌ ያለምንም ጠያቂ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሹራብ እየሰራሁ በመሸጥ እና እራሱ ክር ላቀረበ ለጉልበቴ እያስከፈልኩ የሚያስፈልጉኝ ወጭወቸን ሸፈንኩ። በቅርብ ካወቅኋቸው እሥረኞች መካከል ባልሳሳት ሰኢድ የሚባሉ በነፍስ ማጥፋት ከወረኢሉ የመጡ እስላም አዛውንት አይረሱኝም። ስለሰው ልጅ እና ስለዓለም የነበራቸው አመለካከት እስከዛሬ ድረስ ተማርን ከሚሉ በርካታ ግለሰቦች ካላቸው አመለካከት በጣም የላቀ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በዚህም አባቴን ያስታውሱኝ ነበር።

እሥረኞች እራት በልተን ከተዘጋብን በኋላ አንዳንዴ ሕዝብ “ደህንነት” ተባዮች የተወሰኑ የፖለቲካ እሥረኞችን ጠርተው ማነጋገር እና ያነጋገሯቸውን እሥረኞች ማታውኑ አውጥቶ መግደል የተለመደ ነበር። የካቲት 1978 አንድ ቀን (እረቡ) ከተጠሩት አሥራ ስድስት እሥረኞች መካከል አንዱ ነበርኩ። ተጠራሁ እና ወደ ቢሮ ሄድኩ። አንድ ጎረምሳ ቢሮ ውስጥ ብቻውን ቁጭ ብሎ ይጠብቀኛል። እንደ ገባሁ ዐይኑን ከፊቱ ባስቀመጠው ማስታወሻ ላይ ሰቅሮ ብዙ ጊዜ እንደ ታሰርክ እና ከዚህም እንደ ተማርክ ይገባኛል። ስለዚህ የምታውቀውን ሁሉ ዕውነቱን ንገረኝ እና ነገ ትፈታለህ አለኝ። እኔ ከመጀመሪያው ዕውነቱን ተናግሬያለሁ ስለው ዐይኑን ከማስታውሻው አንስቶ ከጎኑ ባለው መስኮት ወደ ውጭ ወረወረው። ከዚያም አልተማርክም ማለት ነው በል ተመለስ አለኝ። እኔም አይ ይሄን ያክል ታሥሬ ኖሬ ዛሬ በደሌን ሳልናገር አልመለስም አልኩት። አሁንም በመስኮቱ ወደ ውጭ እየተመለከተ ነበር። ንግግሬን በመቀጠል በዕድሜ

የገፉ ድሀ ገበሬወች ልጅ ነኝ። ያለኋቸው ጧሪ ወንድ ልጅ እኔ ብቻ ነኝ። ትምህርቴን ለመጨረስ እየታገልኩ በነበርኩበት ወቅት ትምህርት ቤት በመዘጋቱ ለሥራ ፍለጋ ወደ አሳይታ ስሄድ ደሴ ላይ ካለምንም ጥፋት ታሠርኩ። ከዚህ ጊዜ እስከዚህ ድረስ ወልድያ ከዚህ እስከዚያ ድረስ ደግሞ ደብረ ማርቆስ ነበርኩ። በእነዚይ ጊዜወች እና ቦታወች ምርመራ አድርጋችሁ አንድ ነገር ከተገኘብኝ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ። አሁን ለማለት የምፈልገውን ጨርሻለሁ አልኩት። አንዴ እንኳ ሳይመለከተኝ ዐይኑን ወደ ማስታወሻው መለሰ እና “የገበሬ ልጅ ነኝ አልከኝ” ሲል ጠየቀኝ። አዎ አልኩት። በል ተመለስ አለኝ። እኔም ተመለስኩ እና ለግድያ የምጠራባትን ደቂቃ ቁጭ ብየ ስጠብቅ አደርኩ። ከእኔ ጋር ያነጋገራቸው አሥራ አምስት መሆናቸውን እና ማታውኑ ወስደው እንደገደሏቸው የሰማሁት በማግሥቱ ነበር። ከዚያ በኋላ እኔ የተነገረኝ ነገር ስላልነበረ በግምት ከስምንት ወሮች በኋላ እስከፈታ ድረስ በሥጋት ተውጨ ተራየን ስጠባበቅ ቆየሁ።

ስፈታ አዲስ አበባ ገባሁ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በተፈሪ መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቅቄ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባሁ። አሁንም የፖለቲካ ተሳትፎ አልነበረኝም። ግን እንዳጋጣሚ የብሔራዊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ ፈተና ወስጀ ሙሉ ነጥብ (4.0) በማግኘቴ የቀበሌ ድጋፍ አላስፈለገኝም። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪየን በኢኮኖሚክስ አገኘሁ። ፕሮግራሜን መጨረሻው ተርም ላይ ወደ ማታ ፕሮግራም በማዞር እራሴን ከመንግሥት ምደባ ነፃ አደረግሁ። የመጨረሻ ዓመት (Senior) ተማሪ እያለሁ ከኢትዮጵያ መድህን ድርጅት (Ethiopian Insurance Corporation) ጋር በማናጅመንት አናሊስትነት ተቀጥሬ እሠራ ስለነበር ስመረቅ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተማር ዕድል ቢኖረኝም ከመድህን ድርጅት ጋር መቆየቱን መረጥኩ። ከተመርቅሁ ከአሥራ አንድ ወሮች በኋላ የዓለም አቀፍ የምርምር ማዕከል ተቀላቀልኩ። ከምርምር ማዕከሉ ጋር ለአራት ዓመት ያክል ሠርቸ በግሌ ተጻጽፌ የድህረ ምረቃ ፕሮግራማቸውን እንድቀላቀል ከሥራ ዕድል ጋር ከፈቀዱልኝ አምስት ዩኒቨርሲወች አንዱን መርጬ ወደ አሜሪካ በረርኩ።

የድህረ ምረቃ ትምህርት ዓላማየ በአደጉ (የበለጸጉ ብየ አልጠራቸውም) እና በድሀ አገሮች መካከል ያለውን የተዛባ የንግድ ግንኙነት ለማስተካከል የሚያስችለኝ ጥበብ ለመቅሰም ነበር። የዓለም አቀፍ ንግድን ማዕከል አድርጌ ከንግዱ በፊት የንግድ ሁኔታወችን ለምሳሌ የዋጋ መቀያየርን የሚቀሰቅሱ እንደ ምርታማነት ያሉ ጉዳዮችን ከንግዱም ባሻገር በድሀ አገሮች የመዋዕለ ንዋይን አጠቃቀም ጨምሬ ጥናቴን ጀመርኩ። እየገፋሁ ስሄድ ግን የንግድም ሆነ ሌሎች ፓሊሲወች የሚወሰኑት በፖለቲካ ሰወች እንጂ በኢኮኖሚስቶች አለመሆኑን በመረዳቴ የዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነትን በማስተካከል ድሀ አገሮች እንዲጠቀሙ የማድረግ ዕድሌ የመነመነ እንደሆነ ተረዳሁ።

ስሜቴን ከልጅነቴ ጀምሮ ይከነክነኝ ወደ ነበረው ፍትህን ፍለጋ (search for justice) አዞርኩ። ፍላጎቴ ከስሜቴ ጋር ያልተጣጣመውን ዓለም መረዳት ነበር። ይሁን እንጂ የትምህርቱ ሥርዓት ሶቅራጥስ እንዳለው አስተሳሰብን ለመቀስቀስ እና ለማቀጣጠል (አሳቢወችን መፍጠር) ሳይሆን ባዶ አዕምሮን ለመሙላት የተቃኘ ስለሆነ የፍልስፍናውም ሆነ የፖለቲካ ሳይንሱ ይዘታቸው ስሜት አልሰጠኝም። እራሴን አስተምሬ እንቆቅልሹን እራሴው መፍታት ነበረብኝ።

ምስጢሩ የሕብረተሰብን ዝግመተ ለውጥ (evolution) እና የዝግመተ ለውጡ አሽከርካሪ የሆኑ ማሕበረሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥምር ሁኔታወችን ማጤን እና ሁለንተናዊ የሆኑ ተፈጥሯዊ ሕጎችን መገንዘብ ነበር። አዎ ሕብረተሰብ የተፈጥሮ አካል እንደመሆኑ መጠን ከታሪኩ ጋር ተጣምረው የተከሰቱ ተፈጥሯዊ ሕጎች (Natural laws) አሉት። ሕጎችን ተፈጥሯዊ የሚያደርጋቸው ካለማንም ጣልቃገብነት ሁኔታ የፈጠራቸው በመሆናቸው ነው። እነዚህ ሕጎች በዓለም አካባቢ ባሉ ሕብረተሰቦች በተመሳሳይ ሁኔታወች እና ቅርጽ ይከሰታሉ። ሕብረተሰብ ከታሪኩ ተምሮ በእነዚህ ሕጎች ወይም

መርሆወች ቢመራ ዓለም የሠላም እና የብልጽግና ቋት በሆነች ነበር። ያለያ የተፈጥሮ ስጦታችንን እየቀነስን እና አንድነታችንን እየቦረቦርን በኑሮ ውድነት፣ በአየር ፀባይ መለዋወጥ፣ እና በሠላም እጦት ሳቢያ የሚጠብቀንን ምጻተ መከራ እናፋጥናለን።

ዛሬ በዚህ ግንዛቤዬ ከልጅነቴ ጀምሮ ያብሰለስለኝ የነበረውን ፖለቲካዊ እንቆቅልሽ ለእራሴ በአጥጋቢ ሁኔታ በመፍታቴ ደስተኛ ነኝ። ግንዛቤዬ ከሕይወት ጋር ከተጣመሩ ልምዶች ጋር የሚስማማ በመሆኑ ሃሳቤን የሚጋሩ ሰወች እንዳሉ አልጠራጠርም። በየሕብረተሰቡ ቢያንስ ወሳኝ የሆነ (critical mass) ሕዝብ ነቅቶ ፖለቲካ ለተፈጠረለት ዓላማ ማለት የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ ሲተገበር ለማየት እናፍቃለሁ።

ብርሀኑ አንተነህ

16 የካቲት 2022